ካምደን መማር የሚቻልበት ድንቅ ቦታ ነው። ለልጆች ምርጥ ትምህርት ለመስጠት በየቀኑ ጠንክረው በሚሰሩ ወደር የሌላቸው ትምህርት ቤቶቻችን እና ሰራተኞቻችን እንኮራለን።

እያንዳንዱ የካምደን ልጅ፣ ለመማር፣ ጓደኞችን ለማፍራት እና ለማደግ ምቹ የሆነ፣ ፍላጎቶቹን የሚያሟላ እና በተማሪዎች የተሞላ ክፍል ያለው ትምህርት ቤት በአቅራቢያው እንዲያገኝ እንፈልጋለን።

በካምደን እና በመላው ለንደን የሚገኙ ትምህርት ቤቶች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ የመጣ የገንዘብ ጫና ውስጥ ይገኛሉ።

የወሊድ መጠን መቀነስ እና ቤተሰቦች ከለንደን መውጣት፣ በትምህርት ቤቶች ውስጥ ቦታ የሚይዙ ልጆች ቁጥር እንዲቀንስ ያደርጋል። በዚህም ምክንያት የተማሪዎች ቁጥር እየቀነሰ ነው ትምህርት ቤቶችም ትርፍ ቦታዎች አሏቸው።

በሁሉም ክፍት ቦታዎች አሉ ማለት፡ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ በዓመት በአማካይ 7,500 ፓውንድ፣ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ደግሞ በዓመት በአማካይ 9,700 ፓውንድ የሚሆን ወሳኝ የመንግስት የገንዘብ ድጋፍ እንዲያጡ የሚያደርግ ነው።

እንደ ምክር ቤት፡ በቂ፣ ከፍተኛ ጥራት ያላቸው እና ዘላቂ የትምህርት ቤት ቦታዎች መኖራቸውን የማረጋገጥ እንዲሁም እነዚህን ቦታዎች በብቃት የማስተዳደር ኃላፊነት አለብን።

የተማሪዎች ቁጥር እየቀነሰ በመምጣቱ፣ ይህንን ሁኔታ ከትምህርት ቤቶች ጋር በቅርበት በመስራት ልንፈታው ይገባል።

የ"ትምህርት ቤት አቅርቦት ፕሮግራማችን" አካል በመሆን ባለፈው ዓመት፣በእነዚህ ችግሮች ምክንያት እጅግ ከተጎዱ ትምህርት ቤቶች ጋር በቅርበት ስንሰራ ቆይተናል። ዓላማችንም እነዚህን ተግዳሮቶች ለመቋቋም እንዲችሉ ድጋፍ ማድረግ ነው።

ሁሉም ወገኖች ያሳዩት ቁርጠኝነት ቢኖርም፡ አራት ትምህርት ቤቶች አሁንም በጣም የከበዱ እና ቀጣይነት ያላቸው ጫናዎች እያጋጠሟቸው ነው፤ እነዚህን ጨምሮ፡-

- ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ክፍት ቦታዎች
- የተማሪዎች ቁጥር መቀነስ
- ጥቅም ላይ ያልዋሉ ቦታዎች፡ እና፤
- እየጨመረ የመጣ የገንዘብ ጫና።

ትምህርት ቤቶቹ የሚከተሉት ናቸው፡-

- ሴይንት አልባንስ ቸርች ኦፍ ኢንግላንድ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት
- ሴይንት ጆሴፍስ ካቶሊክ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት
- ሴይንት ፓትሪክስ ካቶሊክ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት
- ላ ሴይንት ዩኒየን ካቶሊክ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

ስለ ቀጣይ እርምጃዎች ለመወያየት ከእነዚህ ትምህርት ቤቶች ጋር በቅርበት ስንሰራ ቆይተናል።

ጥቅምት12 2026 ላይ የእነዚህን ትምህርት ቤቶች የወደፊት ሁኔታ በተመለከተ ምክክር እንዲደረግ ምክረ ሃሳብ አዘጋጅተናል።

ጥቅምት 20 ላይ፣ የካምደን ካቢኔ አባላት—ማለትም ዋናዎቹ የምክር ቤት አባላት—ይህንን ሪፖርት ለመገምገም እና በእነዚህ ምክክሮች እንዲቀጠል ወይ እንዳይቀጠል ለመወሰን ይሰበሰባሉ።

ጥቅምት 21 ላይ፡ ስለተወሰነው ውሳኔ እና ስለሚወሰዱ ቀጣይ እርምጃዎች ለትምህርት ቤቶች እና ለሚመለከታቸው አካላት መረጃ እንሰጣለን።

ምክክርዎቹ የሚካሄዱ ከሆነ፣ ከህዳር 2 እስከ ታህሳስ 14 ባለው ጊዜ ውስጥ ሊከናወኑ ይችላሉ።

በዚህም መሰረት ለእያንዳንዱ ትምህርት ቤት ምክክር ይደረጋል፤ እንዲሁም ቤተሰቦች በተለያዩ አማራጮች ዙሪያ እንዲወያዩ ይደረጋል።

ምክክርዎቹ የሚካሄዱ ከሆነ፣ ለእያንዳንዱ ትምህርት ቤት የቀረቡት አማራጮች የሚከተሉት ናቸው፡-

የሴይንት አልባንስ ቸርች ኦፍ ኢንግላንድ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አማራጮች፡

- በአንድ ክፍል ውስጥ የግድ ገብተው መማር ያለባቸውን ተማሪዎች መጠን (PAN) መቀነስ
- ሴይንት አልባንስን በመዝጋት እና ተማሪዎቹን ወደ ሌላ የካምደን አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በማዛወር፣ ከሌላ ትምህርት ቤት ጋር ማዋሃድ
- ትምህርት ቤቱን መዝጋት

ሴይንት ጆሴፍስ ካቶሊክ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አማራጮች፡-

- በአንድ ክፍል ውስጥ የግድ ገብተው መማር ያለባቸውን ተማሪዎች መጠን (PAN) መቀነስ
- ትምህርት ቤቱን መዝጋት

የሴይንት ፓትሪክስ ካቶሊክ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አማራጮች፡-

- በአንድ ክፍል ውስጥ የግድ ገብተው መማር ያለባቸውን ተማሪዎች መጠን (PAN) መቀነስ
- ሴይንት ፓትሪክስን ትምህርት ቤት በመዝጋት እና ተማሪዎቹን ወደ ሌላ የካምደን አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በማዛወር፣ ከሌላ ትምህርት ቤት ጋር ማዋሃድ
- ትምህርት ቤቱን መዝጋት

የላ ሴንት ዩኒየን ካቶሊክ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አማራጮች፡-

- በአንድ ክፍል ውስጥ የግድ ገብተው መማር ያለባቸውን ተማሪዎች መጠን (PAN) መቀነስ
- ከሌላ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ጋር በፌዴሬሽን መተሳሰር

- ከክፍል 7 እስከ 11 ያለውን ትምህርት ብቻ መዝጋት፤ ነገር ግን ከ16 ዓመት በላይ ለሆኑ ተማሪዎች የሚሰጠውን ትምህርት (ክፍል 12 እስከ 13/14) እንደያዙ ማቆየት እና አወቃቀሩን ማስተካከል
- ትምህርት ቤቱን ከክፍል 7 እስከ 13/14 ያለውን በሙሉ መዝጋት

ምክክርዎቹ የሚካሄዱ ከሆነ፣ እያንዳንዱ ወላጅ እና አሳዳጊ የራሱን አስተያየት መስጠት እንዲችል ለማረጋገጥ በአሁኑ ጊዜ ዕቅድ እያዘጋጀን ነው።

ይህንን መስማት ከባድ እንደሆነ እናውቃለን፤ ነገር ግን ሁኔታው እንዳይባባስ ለመከላከል እንዲሁም ለአሁኑም ሆነ ለወደፊቱ ለሁሉም ልጆች የሚሆነውን ጠንካራ የአካባቢያችንን የትምህርት ለመጠበቅ አሁን እርምጃ መውሰድ አለብን።

ለእያንዳንዱ ትምህርት ቤት የቀረቡ የውይይት አማራጮችን፣ ጥያቄዎችንና መልሶችን፣ እንዲሁም የማግኛ መረጃዎችን ጨምሮ ተጨማሪ ዝርዝሮችን በ **camden.gov.uk/SchoolProposals** ድረ-ገጽ ላይ ያግኙ።

በጥቅምት 21 ሌላ ወቅታዊ መረጃ እናቀርባለን።